# የአክሱማውያን ጎሣ ምን ነበረ?

ሙሉጌታ ውዱ። mooloogeta@hotmail.com

## ስለ ኢትዮጵያ ስፋት መረጃወች

ከዚህ በታች ያሉት መረጃወች በአክሱም ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ ከምን እስከ ምን እንደነበረች በቀላሉና በጥቂቱ ለማሳየት ነው።

በፈረንጆች አቆጣጠር በ1896 ዓ.ም. የየመን ታሪክ ተመራማሪ የነበረው ቴዎዶር ቤንት በስነ መልክአምድር መጽሔቱ የሚከተለውን ፃፈ፦

"ዛፋር [የየመን ከተማ] ዛፋር የሚለው ቃል ትርጉሙ ዋና ከተማ ወይም የመኳንንት ከተማ ከማለት የሚርቅ አይመስልም። ከዚህ በተረፈ የዚች ጥንታዊት ከተማ እውነተኛ ስሟ [ትርጉሙ] ምን እንደሆነ አይታወቅም። ታለሚ (ከ100 እስከ 170 ዓ.ም. ድረስ በእስክንድሪያ የኖረው ሮማዊ ጆግራፈር ክላውዲየስ ታለሚ) ዛፋርን "የአበሾች ከተማ" እያለ ጠራት'።"

በተጨማሪም ቴዎዶር ቤንት እንዲህ ብሎ ጻፈ፦

"ከሃፋ [የየመን ከተማ] አቅራቢያ፣ ከባህሩ አጠገብ፣ የሙቶ ጫማ ያህል ከፍታ ካለው፣ አሁን አሸዋ ቢሞላውም ከባህሩ ጋር በሚገናኘው የውሃ ቋት በተከበበው ሰገነት ዙሪያ የጥንታዊ ከተማ ፍርስራሽ አለ። ከወለሉ ላይ የጥንታዊ ቤተመቅደሶች ቅሪቶች ይታያሉ። የነዚህ ቅሪቶች አርኪቴክቸር ውዲያውኑ በአዱሊስ፣ በኮሎ እና በአክሱም ያሉተን ቤተ መቅደሶች ያስታውሰናል፣ ያለጥርጥርም አንድ ህዝብ እንደሰራቸው መልካቸው ይናገራል።" ቀጥሎም እንዲህ አለ "አሁንም ቢሆን ሰፊ የሆነ ማለቂያ የሌለው ቦታ በእጣን ዛፎች የተሸፈነ ነው። የእጣን ዛፎቹ የአሸር ዛፍ ከመሰለው ከነ ደማቅ አረንጓዴ ቀለማቸውና አነስተኛ ከሆኑ ፍሬዎቻቸው ጋር ሰፊውን ሜዳ ሞልተውታል። ይህ በእጣን ዛፍ የተሸፈነ ሜዳ ከጥንቱ ዋና ከተማ ከዛፋር ጋር የኩሾች ዋነኛ ማእከል ነበር[2]።

የስኮትላንዱ ኦሪየንታሊስት ኮሎኔል ሄንሪ ዩል በ1871 ዓ.ም. በተጻፈው መጽሐፉ እንዲህ ብሎ ፃፈ፦

ቢያንስ ቢያንስ እስከ 10ኛው ምእተ አመት ድረስ በቀይ ባህር ዙሪያ ካሉት ጀምሮ እስከ በርበራ (የሱማሊያ ጠረፍ)፣ እንዲሁም እስከ ሱዋኪን የሱዳን ባህር ጠረፍ ድረስ የአቢሲኒያ ግዛት ነበሩ[3]።

በፈረንጆች አቆጣጠር በ1564 በፖረቱጋሉ አብርሃም ኦርቶሊዮስ የተዘጋጀው የንጉሠ ነገሥቱ የሞዓ አንበሳ ምስል ያለበት የ"አቢሲኒያ" ካርታ እንደሚያሳየውም ፖረቱጋሎች ወደ ኢትዮጵያ እስከመጡበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ እነ ሶማሊያንና እነ ኬንያን ትጨምር ነበረ።




ምስል ፣ የኢትዮጵያ ካርታ። አብርሃም ኦርቶሊዮስ በ1564 ዓ.ም. እንደሳለው።

ከላይ ካየናቸው መረጃዎችና በኢትዮጵያ ካሉ ከቆዩ የጽሑፍ ቅርሶች እንደምንረዳው ከቀይ ባህር ጀምሮ ድሮ የኢትዮጵያ ባህር ይባል የነበረው፤ አሁን የህንድ ውቅያኖስ ተብሎ እስከሚጠራው ባህር ድረስ የኢትዮጵያ ግዛት ነበረ። ያችን ከውቅያኖስ እስከ ውቅያኖስ ድረስ የተደራጀችውን ኢትዮጵያን የገነቧት አክሱሞች (አክሱማውያን) ነበሩ። ለመሆኑ እነዚህ እክሱማውያን እነማን ነበሩ? በውጭ ሰዎች አክሱማውያን የተባሉት ዋና ከተማቸው አክሱም ስለሆነ እንጂ እነዚህ ሰዎች እራሳቸውን የሚጠሩት ኢትዮጵያዊ ብለው ነው። በአክሱም ዐለቶች የተጻፉት የጥንት መልእክቶችና ሌሎችም ቅርሶች እንደሚያሳዩት የአክሱማውያን ቋንቋ ግዕዝ ነበረ። ጎሳ ማለት ቋንቋ ከሆነ የአክሱሞች ጎሳ ግዕዝ ነበረ። ለመሆኑ ግዕዝ ተናጋሪዎች እነማን ነበሩ?

አሁን አማርኛ የሚናገሩት ጎሳቸው በጎሳ ልዩነት አራማጆች 'አማራ' ወይም 'አምሃራ' እየተባሉ የሚጠሩት ከአሰራአምስተኛው ምእተ አመት በፊት የግእዝ ተናጋሪዎች እንደነበሩ የሚያሳዩ ብዙ መረጃወች አሉ። ከግዕዝ ቋንቋም ወደ አማርኛ የተደረገውን ሽግግር የሚያሳዩ መረጃወችም ብዙ ናቸው። ከመረጃወቹ አንዱ ለባህር ምድር ንጉሥ ለዣን ይስሃቅ የተገጠመው መወድስ የሚመስል የአማርኛ ግጥም ነው።

ገጽ ዥን ይስሓቄ ገጽ
በአርያም ይመስል አንቀጽ
እሳት ይመስል ብቁጽ
ከመ መዳልው ልጽሉጽ
ገጹ እንዲያስደነግጽ
እስራኤላዊ መደንግጽ
ዓይነ ቀራንብቱን ቢገልጽ
ማን አየህ ገጽ በገጽ
ዓይን እንደሎሚ ይፍረጽ
ገላው እንደሸንኩርት ይላጽ
ያየህ ገጽ በገጽ
እሳት ይመስል ዣን ተራራ አኂዞ ሲልጽ
ማዕበሉ ሲቆረፅ
እነዲያስደንግጽ ....[4]

ግጥሙ የአማርኛ ይሁን እንጂ ገጣሚው ገና ከግዕዝ ተናጋሪነት ወደ አማርኛ ተናጋሪነት የተሸጋገረ የህዝብ ቋንቋ እንደሚናገር ግልጽ ነው። ብዙ ሌሎች ታሪካዊ ቅርሶችና ጽሑፎችም ተመሳሳይ የሆነ ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተደረገውን ሽግግር ያሳያሉ። ስለዚህ አሁን አማርኛ ተናጋሪዎች እየተባሉ የሚጠሩት ሰዎች የድሮ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው የግዕዝ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ ማለት ነው። የትግርኛ ተናጋሪዎች የድሮ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው የግዕዝ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ ወይ? ከነበሩ ከግዕዝ ወደ ትግርኛ የተደረገውን ሽግግር ፈልገን ማግኜት አለብን። አሁን ትግርኛ የሚናገሩት ሰዎች የድሮ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው የግዕዝ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከነበሩ ጎሳቸው አሁን አማራ ከሚባሉት ጋራ አንድ ነበር ማለት ነው። ሆኖም ግን ይህን ለማለት ከግዕዝ ወደ ትግርኛ የተደረገውን ሽግግር ፈልጎ ማገኜት ያስፈልጋል።

## ስምንተኛው ሺህ

ከግዕዝ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ ሽግግር ለምን አስፈለገ ለሚለው ጥያቄ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቆየው የስምንተኛውን ሺህ ዘመን የተመለከተውን ትንቢት ማየት ያስፈልጋል።

ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች የሚፈሩትና የሚያሰጨንቃቸው ስለ ስምንተኛው ሺህ የሚነገረው ትንቢት ነበር። ከምንም ነገር በላይ ህዘብ፣ ነገሥታትና ካህናት ይህን የስምንተኛውን ሺህ ዘመን ይፈሩ እንደነበር ተጽፈው የቆዩ የታሪክ መዛግብት ሲያሳዩ አሁንም ድረስ ጉዳዩ አፈ ታሪከ ሆኖ ይኖራል። በታሪከ ነገሥት ተጽፈው ከቆዩት ውስጥ በተለይም የአፄ ናዖድ የግዕዝ ዜና መዋዕል ከ1499 ዓ.ም. በፊት አፄ ናኦድ ያደረጉት የፀሎት ልመና ይገኝበታል። አፄ ናዖድ ስምንተኛው ሺህ ዘመን ሳይገባ ውሰደኝ እያሉ አምላካቸውን ይለምኑ እንደነበርና እግዚአብሔርም ሰምቶ የስምንተኛው ሺህ ዘመን ከመግባቱ ከጥቂት ቀናት በፊት እንደወሰዳቸው ተጽፏል።

ስምንተኛው ሺህ ዘመን የገባው 1500 ዓ.ም. ላይ ነው። የሚቆጠረውም አዳም ከገነት ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ሌሎች እንደሚሉት ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም። ከአዳም ኃጢአት በፊት የሰው ልጅ እወቀቱ እግዚአብሔር እንጂ የራሱ የሆነ እውቀት ስላልነበረው ከኃጢአት በፊት የነበረው ዘመን በእግዚአብሔር አቆጣጠር እንጂ የሰው አቆጣጠር ስላልነበረ ዓለም ከተፈጠረ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የሰው ልጅ አያውቅም። አዳምና ሔዋን በጥፋት የተገኘውን እውቀት ይዘው ከገነት ሲባረሩ መጸጸቱን አይቶ እግዚአብሔር ለአዳም ቃል ገባለት፡ እንዲህም አለው። አምስት ቀን ተኩል (አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን) ሲፈጸም ስለ አንተ ከልጅ ልጅህ ተወልጀ፤ሕፃን ሆኘ፤ በምድርህ ድኼ፤ በመስቀል ላይ ተሰቅየ ሞቼ አድንሃለሁ አለው[5]፡፡ ከዛ ጊዜ ጀምሮ እስከ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶሰ ልደት ድረስ 5500 አመት ኾነ። ከጌታችን ልደት እስከ 1500 ዓ.ም. ድረስ 7000 ዓመት ኾነ። አዳም ከተሰናበተ ሰባት ሺህ አመት የሞላው ጊዜ (ሰባት ሺህ አመት ሲጠናቀቅ) ስምንተኛው ሺህ ገባ ይባላል። ይህ ዘመን የገባው በ1500 ዓ.ም. ነው።

ታዲያ ትንቢቱ እንደሚለው ስምንተኛው ሺህ ሲገባ ክፉ ዘመን ይገባል። ጎግና ማጎግ የሚባሉ የክርስቶሰ ጠላቶች ከሰሜን የዓለም ክፍል ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ ምድር ይገባሉ። በእደ ጥበብና በአፋቸው በመደለል ህዝብን ያስታሉ፣ አፋቸውን ከፍተው እግዚአብሔርን ይሳደባሉ፣ ክርሰትናን ለማጥፋትና የኢትዮጵያን ምድር ለመቀራመት ይሰማራሉ። የእደ ጥበብ ሥራቸውን በማየትና ቃላቶቻቸውን በመሰማት ብዙ ህዝብ እያደነቀ ይከተላቸዋል፣ የክርስትና ባህልን ያጠፋሉ፣ ሴቶች እንደ ወንዶች እንዲለብሱ ያደርጋሉ። እግዚአብሔር ባያጠፋቸውና ኢተዮጵያን ባያድናት ኖሮ ጎግና ማጎግ ኢትዮጵያውያንን አጥፈተውና አጨራርሰው ምድሪቷን ወርሰዋት ይቀሩ ነበር። ጎግ ማጎግ አፋቸውን ከፍተው እግዚአብሔርን ስለሚሳደቡና ብዙ ህዝብ ስለሚከተላቸው በተቀደሰው በግዕዝ ቋንቋ እግዚአብሔር እንዳይሰደብ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ከ13ኛው ምእተ አመት ጀምሮ የህዘብ መነጋገሪያ ይሆን ዘንድ አማርኛ ቋንቋን አሰለጠኑ። ህዝብም እነዲለማመደው አበረታቱ። ግዕዝም በቤተ ክህነት ብቻ እየተወሰነ መጣ። ለዚህ ነበር ከግዕዝ ወደ አማርኛ ሽግግር ያስፈለገው። እንደ ትንቢቱ ልክ ስምንተኛው ሺህ ሲገባ ከሰሜን የዓለም ክፍል ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት አውሮፓውያን ነበሩ። የያፌት ልጆች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘፍጥረት ጎግና ማጎግን የያፌት ልጆች ናቸው ይላቸዋል[6]። ሆኖም ግን ወደ ኢትዮጵያ መጀመሪያ የገቡት ፖርቱጋሎች ሰለነበሩና የካቶሊከ እምነት ተከታዮች ስለነበሩ የክርስትና መልክ ነበራቸው። ትህትናም ያሳዩ ስለነበረ በጊዜው የኢትዮጵያ ሊቃውንት የጎግና ማጎግ ክፉ ምልከቶቸን አላዩባቸውም ነበረ። ለዚህ ነው በጥንት መጽሐፍቶች ጎግና ማጎግ ገቡ ተብሎ ያልተጻፈው። ጊዜ እየገፋ ሲሄድ ግን የአውሮፓ ስዎች አፍሪካን በቅኝ ግዛትነት መቀራመት ጀመሩ። የኢትዮጵያን ድንበሮችም ይቀራመቱ ጀመር። መሃል ኢትዮጵያ ሲገቡ እግዚአብሔር ጣላቸው። እነደገናም ከአውሮፓ መጥተው አሜሪካ በሰፈሩ "እኛ ሰላም እናወርዳለን" በሚሉ አውሮፓውያን መሪነት አውሮፓውያን አንድ ልብ ሆነው ኢትዮጵያውያንን በማስራብ፣ ኢትዮጵያን በመበተን፣ ህዘቦቿን

በማናከስና ኃይማኖቷን በማጥፋት እኩይ ሥራ ላይ እነሆ እስካሁን ድረስ ተሰማርተዋል። በርዕዮተዓለማቸውም ህዝብን ሁሉ አስክረዋል። በወኪሎቻቸው በኩል ኢትየጵያን ጭራሽ ሊያፈራርሷት ተቃርበዋል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል ትድናለች። የአውሮፓ ሰዎች ኢትዮጵያ ከገቡ ከዛሬ አምስት መቶ አመት ጀምሮ ኢትዮጵያ እያሽቆለቆለች፣ እየመነመነችና እየጠፋች ነው የመጣችው። ከማሽቆልቆል የዳነችበት አንድ ዘመን ቢኖር አፄ ፋሲል ከነገሡበት ከመስከረም 1625 ዓ.ም. ጀምሮ ለሚቀጥሉት አንድ መቶ ሰላሳ ስድስት አመታት እስከ ዘመነ መሳፍንት ድረስ በኢትዮጵያ የታላቅ ብልፅግናና የተደላደለ ኑሮ ዘመን ነበረ። አፄ ፋሲል ፈረንጆች ሞምባዛ ላይ የሰሩትን ግፍ ከሰሙና በኢትዮጵያም ያስከተሉትን ችግር ካዩ በኋላ አንድም ሳይቀር ፈረንጅን ከኢትዮጵያ ምድር በማስወጣታቸው ኢትዮጵያውያን ፈረንጅ በሚዘራው መርዝ ሳይናቆሩ ፋታ አግኝተው አምላካቸውን እያመስገኑ የራሳቸው በሆነ የግንባታና የምርት ሥራ ተሰማርተው ይኖሩ ነበረ። ይሁንና በመጽሐፍና በኢትዮጵያ ክርስትና ሕግ መሠረት ንጉሠ ነገሥት ስለማይገደልና ግንቦት አንድ 1761 ዓ.ም. አፄ ኢዮአስ ቀዳማዊ በራስ ሚካኤል ትእዛዝ ሲገደሉ ይህ ህግ ስለተሻረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን በዘመነ መሳፍንት ቀጥቷታል። የዛሬ አርባ ሶስት አመትም አፄ ኃይለስላሴ ስለተገደሉ እነሆ ዘመነ መሳፍንትን የመሰለ አርባ ሶስት የጥፋት አመታትን እስካሁን አሳልፈናል።

በኢትዮጵያ ላይ የምእራባውያን በተለይም የአሜሪካ ፖሊሲ ኢትዮጵያን መበታተን ነው። ምእራባውያን የአሜሪካ አጋሮችም የዚህ ፖሊሲ ተባባሪ ናቸው። ለምሳሌ ቁቤ የሚባለውን በላቲን ፊደል መጻፍ ለኃይሌ ፊዳ ያቀርቡላቸው ጀርመኖቸ መሆናቸውን ፈርነሳዊቷ የኃይሌ ፊዳ ባለቤት በቅርቡ ለሸገር ራዲዮ በሰጡት ቃለ መጥይቅ ገልፀዋል። ፈረንጆች ኦሮሞዎች በላቲን ፊደል እንዲጠቀሙ ሲያነሳሷቸው የግእዝ ፊደል ከሳባ ፊደል የመጣ ነው እያሉ የሳባ ፊደል ደግሞ የዐረብ ፊደል እንደሆነ አስመስለው ነው የሚነግሯቸው። የሳባ ፊደል የኩሽ ፊደል መሆኑን ይደብቋቸዋል። ታዲያ ፈረንጅ የሚያመልኩ አንዳንድ ፖለቲከኞች የሳባ ፊደል የኩሽ ፊደል መሆኑን ስለማያወቁና በመራራ የበቀል መንፈስ ተነሳስተው የላቲን ፊደል ይሻለናል እያሉ ህዝብን አሳስተዋል። ኦሮሚያ የሚባለውን ስምና ካርታም ያዝጋጁት ጀርመኖች ናቸው። ባለፈው ጊዜም የኦሮሞ እንቀስቃሴ አዝማሚያ ኢትዮጵያን የሚያፈርሳት መስሎ ሲታያቸው የጀርመኑ ቻንስለር አንጀላ መርከል ባለፈው አመት በጥቀምት ወር የተከልነው መርዝ ፍሬ አፈራ ብለው ለአጋሮቻቸው የደስታ መልእከት ለማስተላለፍ አዲስ አበባን ጎብኝተው ነበር። ጀርመኖቸ ይህን የሚያደርጉት በኢትዮጵያ መበታተን ከምርኮው ቤታቸውን ለመሙላት ነው። የአሜሪካን ስራ በተመለከተ በርካታ ልዩ ልዩ ማሰረጃዎችና የአምባሳደር ኸርማን ኮኸን መጽሐፍና[7] ፤ እንዲሁም እኒሁ ሰው በሃፍት ፖስት የዜና ጣቢያ የሰጡት ቃል[8] ምስክር ሆኖባቸዋል። እንደ አውሮፓውያነ አቆጣጠር አርብ ቀን ዲሴምበር 10 ቀን 1976 ዓ.ም. የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሄንሪ ኪሲነጅርና የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሊዊስ ዲጉሪነጓድ ብራሰልስ ውሰጥ ባደረጉት ሰበሰባ ጂቡቲ ተመልሳ የኢትዮጵያ አካል እንዳተሆንና የፈረንሳይ ወታደሮች ጅቡቲ እንዲቆዩ እና ጅቡቲ በኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ተሰባ እንዳትገባ የጅቡቲን ህዝብ ለመቀለብ በአመት ከ20 እስከ 30 ቢሊዮን ዶላር ለመመደብ ተነጋገሩ[9]። አሜሪካኖቸ ይህን እያደረጉ በሌላ በኩል ደግሞ ኤርትራን በመገንጠል ኢትዮጵያ ያለ ባህር በር እንድትቀርና በኋላም እንድትበታተን የስለላ መረባቸውን በሰፊው ዘርግተው ሲሰሩ ኖረዋል። ከአድዋ ጦርነት ወዲህ በተለይም ከዛሬ ሰባ አመት ጀምሮ በፈረንጆች የሚፃፉ መፃሕፍት እያንዳንዱ አረፍተ ነገርና የቃላት አጠቃቀም ኢትዮጵያን በመበተን ላይ ያነጣጠረ ነው። አሜሪካኖች ፖሊሲያቸውን ከኢትዮጵያውያን በሚመጣ ማመልከቻ አይቀይሩም። ድርሻው የኢትዮጵያውያን ነው - ሰላምን ከእግዚአብሔር እጅ ሊሿት ይገባል።

## ጎሣና ክርስትና

የክርስትና እምነት በጎሣ መከፋፈልን (እኔ ኦሮሞ ነኝ፣ እኔ ትግሬ ነኝ፣ እኔ አማራ ነኝ ማለትን) ይጠየፋል። እግዚአብሔር በክርስትና አንድ ያደረገውን ህዝብ በጎሣ አሰተዳደር መለየት ክርስቶስን ያሰቀይማል። ይህም በአዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ ማሰጠንቀቂያ ተጽፏል[10]። ጎሣ ከክርስትና በታች ነው። በእስልምና እምነትም ቢሆን መሐመድ በጎሣ መከፋፈልን አውግዟል። ከእስልምና በፊት ዐረቦች ቁሬሽ፣ ባኑ ሃሺም፣ ባኑ ኡማያ ወዘተ በሚባሉ ብዙ ጎሣዎች ተከፋፍለው "ይህ ጎሣ ከኔ ክልል አይድረስ፣ አንተ ከኔ ክልል አትደረስ" እየተባባሉ እርስ በርስ ይዋጉ ነበር[11]። መሐመድ በጎሣ መከፋፈልን አስቆመ። ይህን የጎሣ ክፍፍል ዘመን የጨለማው ዘመን ወይም ጃሂሊያ ብሎ ጠራው። ህወሃት ያመጣው ብሄር ብሄረሰብ የሚባል የጎሣ ክፍፍል ኢትዮጵያን አንድ ሺህ አራት መቶ አመት ወደኋላ ወስዶ አረቦች ጃሂሊያ የሚሉት የጨለማ ዘመን ውሰጥ ጨምሯታል። ታዲያ ዐረቦች ለሳውዲ ዐረቢያ በጎሣ መከፋፈልን የሚከለክል አንድ የእስልምና ህግ አውጥተው ይህን እስልምና ወደ ኢትዮጵያ ሲያመጡት ኢትዮጵያውያንን በጎሣ ተከፋፈሉ ሊሉ ይችላሉን?

## በደቡብ ያሉ ኢትዮጵያውያን አከሱማውያን ነበሩ ወይ?

ከላይ እንዳየነው ቀደም ሲል ኢትዮጵያን ከውቅያኖስ እስከውቅያኖስ በግንባር ቀደምነት የገነቧት የግዕዝ ተናጋሪዎች ቢሆኑም በደቡብ የሚኖሩት ተሳታፊና ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው ምክንያት አክሱማውያን ነበሩ። ኬንያም ሆነ ቦረናም ሆነ ሶማሊያም ሆነ ዝዋይ ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ አካል ስለነበሩ አክሱማውያን ነበሩ። ከአክሱም ሥርወ መንግሥት ህልፈት በኋላ ግን የግዕዝ ተናጋሪዎች ተዋናይ ገንቢዎች ቢሆኑም አዲስ በተተካው በበግወና ሥርወ መንግሥት ለሶስት መቶ ሃምሳ አመታት አገዎች የመሪንቱን ቦታ ይዘው ኢትዮጵያን መገንባታቸው ይታወሳል። የሐድያ ንጉሥ የመሐመድ ልጅ ንግሥት ኢሌኒ ነገሥታትን ማውረድና ማሾም የሚያስችል ስልጣን እንደነበራቸው በታሪክ ነገሥት ሠፍሮ ይገኛል። በተለይ ከፊል ኦሮሞ ከሆኑት ከአፄ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ በአህመድ ግራኝና በኋላም በዘመነ መሳፍንት የመነመነችውን ኢትዮጵያ መልሰው በግንባር ቀደምነት ያቀኗት ኦሮሞዎች ነበሩ። ኦሮሞዎች በዳር ድንበር ጥበቃ ተሳትፎ የጀመሩት ወደ ማሃል አገር ከመግባታቸው በፊት በአፄ ሰርፀድንግል ዘመነ መንግሥት ወደ ባህረ ነጋሽና ወደ ምፅዋ በቱርኮች ላይ የዘመቱ ጊዜ ነው። በዛን ጊዜ ብዙ የኦሮሞ ወታደሮች ትዳር እየመሠረቱ በኤርትራና በትግራይ አካባቢ እንደቀሩ ይነገራል። አሁን አያቶቻቸው ኦሮሞ መሆናቸውን የማያወቁ ብዙ ሰዎች በኤርትራና በትግራይ ይኖራሉ ማለት ነው። ኦሮሞዎች ወደ ማሃል አገር ከገቡ በኋላ ኢትዮጵያን በንጉሠ ነገሥትነት ሲመሩ አንድ መቶ አመት እንኳን አልሞላቸውም ነበር። በጎንደር ሥርወ መንግሥት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ኦሮሞው አፄ ኢዮአስ (አድያም ሰገድ) የጦር መኮንኖቻቸውና በዙሪያቸው የነበሩት ታማኞቻቸውና ወታደሮቻቸው ኦሮሞዎች ስለነበሩ በሳቸው ዘመን ጎንደር በኦሮሞዎች ተሞልታ ነበር። ጎንደር ውሰጥ ኦሮሞዎች እንደኖሩባት የሚታወቀው በጎንደር አማርኛ ውሰጥ ብዙ የኦሮምኛ ቃላቶች እንዳሉ በማስተዋል ነው። ለምሳሌ ጨቅላ፣ ሙጫ (ሙ እና ጫ አይጠብቁም) እና ሌሎችም ይገኙበታል። በጎንደር አማርኛ ውስጥ ምን ያህል ኦሮምኛ እንዳለ የቋንቋ ባለሙያወች ቢያጠኑት መልካም ሳይሆን አይቀርም።

አፄ ምኒልክ ኦሮሞ ስለነበሩና እንደሳቸው ኦሮሞ የነበሩት አፄ ኢዮአስ በታዋቂው የትግራይ መስፍን በራስ ሚካኤል ስሁል እንዴት እንደተገደሉ ስለሚያሰታውሱና ከአፄ ዮኃንስ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ስለሚያውቁ ከሰሜን መሳፍንቶች ይርቁ ነበር። እምነታቸውም በኦሮሞዎች ላይ እንደነበር የጦር መኮንኖቻቸውና ዋና ባለሰልጣኖቻቸው ብዙዎቹ ኦሮሞዎች መሆናቸውን በማየት መረዳት ይቻላል። ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጠመንጃ የሚይዙ ነፍጠኞች ሆነው ቢኖሩም የጦር መሪዎቹ ግን ኦሮሞዎች ነበሩ። እነዚህ የጦር መሪዎች ኢትዮጵያን መልሶ ለማቅናት እንቅፋት የሆናቸውን ኦሮሞም ይሁን ሶማሊም ይሁን ሐረሪ ውጊያ ይገጥማሉ። የኢትዮጵያ መሠረቷ በክርስትና ላይ የተገነባ በመሆኑና በክርስትና እምነት እራስን በጎሣ መለየት ውግዝ ስለሆነ እኔ ኦሮሞ ነኝ፣ እኔ አማራ ነኝ አይሉም ነበር። ስማቸውም የክርስትና ስም ስለነበር ከየት ጎሣ እንደሆኑ ለማወቅ አስቸጋሪ ነበር።

## *መደምደሚያ*

ህዝባዊ ወያን ሃርነት ትግራይ የሚባለው ድርጅት በውጭ ሃይሎች ተቀጠሮ በኢትዮጵያ ህዝብ መካከል የጥላቻ ግድግዳወችን ተክሏል። ስድሳ ሺህ የትግራይ ወጣቶችን የጨረሰውና ያስጨረሰው ኤርትራን ለማስገንጠልና ኢትዮጵያን ለመበተን እንጂ ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት አልነበረም። ከውጭ በታዘዘው መሠረትም ክርስትናን ለማጥፋትና ለመሬት ንጥቂያ ዋና ጠላቴ አማራ ነው ብሎ ተነስቶ አማራ በሚላቸው ላይ ለማየትና ለመስማት የሚዘገንኑ ግፎችን ለሃያ ሰባት አመት ፈፅሟል። ድሮ ክርስቲያን የነበሩትና ኢትዮጵያን ይወዱ ይመስሉ የነበሩት የትግራይ ሰዎች ብዙዎቹ ለክርስትናም ሆነ ለኢትዮጵያ ግድ ያላቸው አይመስልም። እንዲያውም ክርስቶስን አናውቀውም ክርስቲያን አይደለንም፤ ኦሪታውያን ነን የሚል እንቅስቃሴ ጀምረው ብዙ የትግራይ ሰዎች በደስታ ተቀላቅለዋቸዋል። የትግራይ ህዝብ አይኑን መግለጥ አለበት። ሰይጣንን እየተከተለ መሆኑን አውቆና ነቅቶ ፍቅሩን ወደ ኢትዮጵያ ማዞር አለበት። የሃገር ኑሮን በዘር ማስላት በየትኛውም አኪያሄድ የውድቅት መንገድ ነው። የውጭ ሃይሎችን ሴራ እና እንደ ህወሃት ያሉትን ቀማኛ ቡደኖች በተመለከተ ቅዱስ መጽሐፍ ለትግራይ ሰዎች ማስጠንቀቂያ የሰጣል፦

"ልጄ ሆይ፥ ኃጢአተኞች ቢያባብሉህ እሺ አትበል።
ደምን ለማፍሰስ ከእኛ ጋር ና እናድባ፥ ለንጹሕም ያለ ምክንያት ወጥመድን እንሸምቅበት ቢሉ፤
በሕይወታቸው ሳሉ እንደ ሲኦል ሆነን እንዋጣቸው፥ በሙሉም ወደ ጉድጓድ እንደሚወድቁ ይሁኑ፤
መልካሙን ሀብት ሁሉ እናገኛለን፥ ከምርኮውም ቤታችንን እንሞላለን፤
ዕጣህን ከእኛ ጋር ጣል፤ ለሁላችንም አንድ ከረጢት ይሁን ቢሉ፤
ልጄ ሆይ፥ ከእነርሱ ጋር በመንገድ አትሂድ፥ ከጎዳናቸውም እግርህን ፈቀቅ አድርግ፤
እግሮቻቸው ወደ ክፋት ይሮጣሉና፥ ደም ለማፍሰስም ይፈጥናሉና።
መርበብ በወፎች ዓይን ፊት በከንቱ ትተከላለችና።
እነርሱም በደማቸው ላይ ያደባሉ፥ በነፍሳቸውም ላይ ይሸምቃሉ።

እንዲሁ ይህ መንገድ ትርፍን ለማግኘት የሚሳሳ ሁሉ ነው። የባለቤቱን ነፍስ ይነጥቃል[12]።"

ክላይ እንዳየነው አክሱማውያን በዘር መከፋፈልን አያውቁም ነበር። የትግራይ ሰዎች ከጥንት ጀምሮ የአክሱም ሰዎች ከነበሩ ከክርስትናና ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ የጎሳ ፍቅርን ከየት አመጡት? የትግራይ ሰዎች ከጥንት ጀምሮ የአክሱም ሰዎች ከነበሩ ኢትዮጵያን ከመገንባት ይልቅ ኢትዮጵያን ማፍረስን ከየት አመጡት? ፈረንጆች ክኢትዮጵያ ሰዎች ውስጥ እነደ ትግርኛ ተናጋሪው የሚገቁት ሰው የለም ምክንያቱም ኢትዮጵያ ውስጥ የፈለጉትን ለማድረግ ትንሽ ዶላር ለትግሬዎች መስጠት ይበቃል ይላሉ። በዊኪሊክስ በኩል የተጋለጠው አስተያየታቸው ይህን ይመሰክራል። ሌላው ቀርቶ የግበፅ ባለስለጣኖች ይፋ በወጣው ስበሰባቸው "ኤርትራ ነጻ የወጣችው ኢትዮጵያን በማነቆ ለመያዝ እኛ እንድንገለገልባት አይደለምን?" አሉ በውሰጠ ታዋቂነት የህወሃትን ታሪክ ሲናገሩ ደግሞ "ኢትዮጵያ ትንሽ ዶላር ሲስጧቸው አገራቸውን አፍርሰው ለውጭ ሰዎች የሚያሰርከቡ ሰዎች ያሉባት የአፍሪካ አገር ናት። እኛ ኦሮሞዎችንና የኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅትን መጠቀም እንችላለን" አሉ። ግብፆች የሜኔሶታ ኦሮሞዎችንና ኦነግን ሊጠቀሙ ቢሞክሩም ኢትየጵያ ያሉት ኦሮሞዎች ግን አያቶቻችን አጥንታቸውን የከሰከሱባትን፣ አባቶቻችን የገነቧትነ አገር አፍረስን ለማን ነው የምናስረክበው? በማለት ኢትዮጵያን በማፍረስ ላይ ተባባሪ አንሆንም ብለዋል። ኦሮሞዎቸ አሰተዋሉ። ጥበብ ለምን ከትግሬዎቸ ራቀች? ለትግራይ ሰዎች ከኢትዮጵያዊነት የበለጠ ክብር የለም። ኣረ ስለ እግዚአብሔር ወደ አዕምሯችሁ ተመለሱ!

እግዚአብሔር ምህረቱን ከኢትዮጵያ አይለይብን።

የካቲት 10 ቀን 2010 ዓ. ም.

[1] Quoted in 1912 by Wilfred H. Schoff, Secretary of the Commercial Museum, Philadelphia

[2] Ditto

[3] Yule, Colonel Henry. "The Book of Ser Marco Polo" (Vol. II, p. 434). London. John Murrat. 1871

[4] ተክለ ጻደቅ መኹሪያ ታሪክ ነገሥትን ጠቅሰው "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለው መጽሐፋቸው እንዳሰፈሩት።

[5] መጽሐፈ አክሲማሮስ

[6] ኦሪት ዘፍጥረት ም 10፡ 2

[7] Herman J. Cohen. Intervening in Africa: Superpower Peacemaking in a Troubled Continent

[8] Herman Cohen Statement on Huff Post Live 01.23.2013፡ "During the conflict with Ethiopia the one country Eritrea (Isaias Afeworki) trusted was the United States.  This goes back historically because of everything we did to help them get independence. They think the US betrayed them by favoring with Ethiopia."

[9] Foreign Relations, 1969-1976, Volume E-6, Documents on Africa, 1973-1976

[10] ወደ ገላትያ ሰዎች 3፡28፣ 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎቸ 12፡13፣ ወደ ቆላስይስ ሰዎች 3፡11፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2፡14

[11] Grunebaum, G. E.: Classical Islam - A History 600-1258 - 1970

[12] መጽሐፈ ምሳሌ ም1፡ 10